EthioLion

# እህትክን፣ እህቴን፤

ካልተሰማህ ጩኸቷ የእህት ደካማዋ

ያቅመ ቢሷ ረዳት የለሽ ከልታማዋ

ወይኔ ስትል ተጠቅታ ..

ደክማ አብቅታ ተዘግቶ ልሳኗ፤

ሲቆለመም አንገቷ ሲታጠፍ አንጀቷ፣

የዚያች ኢትዮጲአዊት ካልተሰማህ ጣሯ.

በሳውዲ፣ በሊባኖስ በሊቢያ …

በየአረብ አገሩ የእህቶቻችንን ጣር መከራ

ሰምተህ በቃ ካላልክ  ደምህ ካልፈላ፣

ነደህ አመድ ሁነው በውስጥህ ዝምታ።

እንዴት ነው ሚቻለው ከዚህ በላይ መኖር፤

በዐይነ-ሥጋ ማየት በጆሮ ማዳመጥ፤

እህት ስታለቅስ ወዮው ወይኔ ስትል፤

አረመኔ ጅቦች ሲረባረቡባት

የጣር የሰቀቀን ድምጿ ሲመላለስ፣

የግፍ ትዕይንት ማየት አዕምሮ አልችል ሲል፤

መኖር ከተቻለ ቀንን በቀን ማደስ፤

ኑሮን ተርጉሙልኝ፣ ምንድነው ሕይወትስ?!

ቁመን እያየናት ዋይ! እያለች እሷ …

አንገቷን ቆልመው አንጀቷን አጣጥፈው፤

እንደ ቄራ ሥጋ ከትክተው ሰባብረው፤

እህትክን፣ እህቴን …

ሊካፈሏት ጫኗት በመኪና ወስደው።

እሳቱ ቃጠሎው ሀገር አስመርሯት፣

ይሻል እንደሁ ብላ ስትኖር በስደት፣

ያልተወለደ አንጀት የባሰ አጋጠማት፣

ሰብአዊነት ጠፍቷል ተወራረዱባት፣

ለዚህች ለተገፋች እረ ማን አዝኖላት?!

እረ ወገን ስማ .. እረ ሕዝብ ቁረጥ፣

ከሰው በታች ወርደህ እንሰሣ ሁነሃል፣

ሙክቱ ሠንጋቸው ሚገርፉህ ሚነዱህ፣

ሚጠጡህ ሚበሉህ የሚቦጫጭቁህ፣

ይህን እምብኝ ብትል ምን ይቀርብሃል?!

እረ መሪ ውጣ ለሕዝብ ሕይወት ስጥ፤

ካላለቅስክ አልቅስ ካልነደደህ ንደድ፣

ምክር ተመካከር አብር አስተባብር፣

ለኩስ ቀንዲልህን ሁሉም ይመልከተው፣

መብራት ሁን ለሕዝብ ይገለጥ ጨለማው።

……….///………..

ታከለ ረታ

Ethiopia Will Prevail!